በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!! ኒቆዲሞስ

እንኳን ለአቢይ ጾም ሰባተኛ ሳምንት በሰላም አደረሳችሁ!!!

የዚህ ሳምንት ስያሜ ኒቆዲሞስ ይባላል። ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን ሲሆን የአይሁድ አለቃ፣ የእስራኤል መምህርና የኦሪት ምሁር /ዮሐ 3÷1፤ 3÷10፤ 7÷51/ ነበር ። ኒቆዲሞስ ፈሪሳውያንን ፈርቶ የአይሁድ አለቃም ስለሆነ አይሁድ ከሚቃወሙት መሲህ ጋር ከታየ እርሱንም ሊቃወሙት ስለሚችሉ በሌሊት እንጂ በመዓልት፤ በጨለማ እንጂ በብርሀን ወደመሲሁ መሄድ አልቻለም። ቢሆንም ይህ ፍርሃት የጌታን ትምህርት ከመማር አላገደውም፤ በሌሊት ብርሀን ወደ ሆነው ክርስቶስ መጣ። ከዚያም በኋላ በዮሐ 7÷51 ላይ እንደምናገኘው በድፍረት ስለጌታ ባይመሰክርም አይሁድ በክፋት ተነሳስተው ጌታን ሳይመረምሩ እንዳይፈርዱበት ግን አሳስቧቸዋል።

ምስባክ ፡ መዝ.16: 3 ትርጉም፦

ሐወጽከኒ ሌሊተ ወፈተንኮ ለልብየ፤ በሌሊትም ጐበኘኸኝ ልቤንም ፈተንኸው፤

አመከርከኒ ወኢተረክበ ዓመፃ በላዕሌየ። ፈተንኸኝ፤ ዐመፅም አልተገኝብኝም። ከመ

ኢይንብብ አፋየ ግብረ እጓለ እመ ሕያው። የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው።

በዚህ ሰንበት የሚነበበው ወንጌል የዮሐንስ ወንጌል 3÷ 1-11 ሲሆን የኒቆዲሞስንም ታሪክ የምናገኘው በዚህ የመጽሃፍ ክፍል ነው። "ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ። እርሱም በሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ መጥቶ እንዲህ አለው..."

ኒቆዲሞስ ትንቢተ ነቢያትን የሚያውቅ ፈሪሳዊ እንዲሁም ከጌታ ዘንድ በማታ በመመላለስ የተማረ ቢሆንም ለመረዳት ያስቸገረው አንድ የጌታ ትምህርት ግን ነበር፤ ይህም "የሰው ልጅ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልገዋል" የሚለው ትምህርት ነበር። ጌታንም “ሰው ካደገ በኋላ እንዴት ወደ እናቱ ማህጸን ተመልሶ ሊወለድ ይችላል?” በማለት ጠይቆታል። ጌታም “ከውሃና ከመንፈስ ትወለዱ ዘንድ አላችሁ” በማለት በጥምቀት የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን አስተምሮታል። /ዮሐ 3÷ 17/ አንድ ሰው በስጋ ከወላጆቹ ሳይወለድ በዚህ አለም መኖር እንደማይችል ሁሉ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ያልተወለደም በመንፈሳዊው አለም መኖር አይችልምና። ከኒቆዲሞስ ምን እንማር?

1. አትጎቶ ርእስን /ራስን ዝቅ ማድረግን/፡- የምናውቅ ቢመስለንም ገና ብዙ የማናውቀው አለና በትህትና ከታላላቆቻችን ስር ሆነን ልንማር ይገባል። ኒቆዲሞስ ፈሪሳዊ መምህር ነኝ ብሎ በልቡ ስለተፈጠረበት ጥያቄ ከጌታው ከመማር ወደኋላ አላለምና፤ ለሚታበዩ አዋቂ ነን ባዮች ማስተማርያ ሆኗል
2. ትግሃ ሌሊትን /በሌሊት መትጋትን/፡- ቀን አይሁድን በመፍራት ባይማርም በሌሊት ግን ፊጽሞ ሳይታክት ይመላለስ ነበር፤ በዚህም ለምስጢረ-ጥምቀት መገለጥ ምክንያት ሆነ
3. እስከ መጨረሻ መጽናትን፡- ጌታን ካገኘባት ሰዓት ጀምሮ በሌሊት የተመላለሰው ኒቆዲሞስ እስከመጨረሻው በጌታው በማመኑ በዕለተ አርብ የጌታውን ስጋ ከዮሴፍ ዘአርማትያስ ጋር ከመስቀል አውርዶ በአዲስ መቃብር እያመሰገነ ለመቅበር በቅቷል። ጌታም ምን ብለው ሊገነዙት እንደሚገባ የነገራቸውን ምስጋና "ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ህያው ዘኢይመውት....." ቤተ-ክርስቲያንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ጌታዋን ስታመሰግንበት ትኖራለች

እንግዲህ እኛ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ከኒቆዲሞስ ህይወት እነዚህንና ሌሎች ብዙ ቁምነገሮችን እንማራለን። የኒቆዲሞስ በሌሊት ገስግሶ መምጣት ለምስጢረ ጥምቀት ትምህርት መገለጥ ምክንያት እንደሆነ ሁሉ በቅዳሴው፣ በኪዳኑ፣ በሰዓታቱና በማኅሌቱ መገኘትና መሳተፍ ረቂቅ የሆነው ሰማያዊ ምሥጢር ፍንትው ብሎ እንዲገለጥልን ያደርጋልና በምሥጢራት በመሳተፍ ራስን ዝቅ በማድረግ ለታላቅ ክብር እንድንበቃ የጌታ መልካም ፈቃድ ይሁንልን። ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር !!! ይቆየን!

ቅ/ጳ/ህ/ግ/ጉባኤ ትምህርት ክፍል መጋቢት ፲፯ ፪ሺ፲